7. የሚሊሺያን የሰው ኃይል ይመለምላል፣ ያሰለጥናል፣ ያደራጃል፣ ያስታጥቃል፣ ያሰማራል ያሰናብታል፤
8. የሚሊሺያ አባላትን ብቃት ለማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግንባታን ሥራ ከሚመለከተው አካል ጋር ያስተባብራል፤
9. ወንጀል እንዳይፈፀም ይከታተላል፣ ይከላከላል፣ ይቆጣጠራል ከህዝባዊ ፖሊስ ጽህፈት ቤት ጋር በመተባበር የአካባቢ ፀጥታ ኃይል ጋር ይሰራል፤
10. ሚሊሺያው ከምርት ተግባሩ ሳይነጠል በአካባቢው በሚካሄደው ፀጥታ የማስከበር እንቀስቃሴዎች ከህዝባዊ ፖሊስና ከህዝብ ጋር የሚሰራበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣ ይቆጣጠራል፣ ለረጅም ጊዜ ከምርት ሥራ የሚነጥል የፀጥታ ሥራ እንዳይሰማራ ይከታተላል ፣ይቆጣጠራል፤
11. ለአገር ሠላምና ደህንነት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአገር መከላከያ ሠራዊት ጋር ይሰማራል፤
12. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ አስከባሪ አካላት ዲሞክራሲያዊ አመለካከታቸው እንዲዳብርና በሕገ-መግንስትና በሰብዓዊ መብቶች ረገድ ግንዛቤያቸውን ለማሳደግ ይሰራል፤
13. የፀረ-ሠላም ኃይሎችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ በዚህም የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ አሰራሮችን አጥንቶ ተግባራዊ ያደርጋል፤
14. በክልሉ ውስጥ ባሉ አስተዳደር እርከኖች መካከል የሚነሱ የማካለል ጥያቄዎች በሠላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፤
15. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋዎች በአስቸኳይ በቁጥጥር ሥር ለማዋል እንዲቻል ሲታዘዝ የፀጥታ ኃይል ያሰማራል፤
16. የፀጥታ መደፍረስ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት በሚወስደው የመከላለል እርምጃ በሴቶች በህፃናት ላይ ጉዳት እንዳይርስ የጥንቃቄ እርምጃ ይወስዳል፤
17. ከተለያዩ ኃይማኖትና እምነት ተከታዮች መካከል ሠላምና መከባበር እንዲሰፍን ለማድረግና ግጭትንም ለመከላከል እንዲቻል አግባብ ካላቸው የመንግስት አካላት፣ የኃይማኖት ተቋማትና ከሌሎች ማናቸዉም አካላት ጋር ተባብሮ ይሰራል፣ የኃይማኖት ተቋማትን ይከታተላል፣ ከፌዴራል ህጋዊ እዉቅና ያገኙትን ይመዘግባል፤
18. ከሚመለከተው የመንግሥት አካል የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 19
## የባህልና ቱሪዝም ቢሮ

ቢሮዉ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

17.በመንግሰትም ሆነ በግሉ ዘርፍ የማስታወቂያና የፕሮሞሽን ስራዎችን በተመለከተ ከሚመለከተዉ አካል ጋር በመሆን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ ፈቃድ ይሰጣል፣ይሰርዛል፣ያድሳል፤

18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

19. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚረዱ ሌሎች ተግባሮችን ያከናዉናል፡፡

**<u>አንቀጽ 28</u>**

**<u>የአካባቢ፣ደንናየመሬት አስተዳደር ቢሮ</u>**

ቢሮዉ የሚከተሉ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በ□ዴራል የአካባቢ ፖሊሲ ላይ ተመስርቶ የክልሉን የአካባቢ ሕጎችና ስልቶችያዘጋጃል፣ ሲ□□ቅም በሥራ ላ□ እንዲውሉ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸዉንም ይከታተላል፤
2. በ□ልሉ □ስ□ በሚካሄድ የልማት ፕሮጀክቶች፣ ፖሊሲዎችና ስልቶች ላይ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤
3. የማህበራዊና ኢኮኖማያዊ ልማት ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ የሚኖራቸው ጉልህ ተፅዕኖ□እንዲገመገም ከፕሮጀክቱ አቅራቢዎች የአካባቢ ተፅዕኖ ዘገባ □እንዲቀርብ ያደርጋል፣ ዘገባዎችን በመመርመር የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ አፈፃፀማቸውን ይከታላል፣ □ቆ□□ራል፤
4. የማህበራዊና የኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ኅሕጎች፣ ዕቅዶችና መርሀ-ግብሮች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ከአካባቢ ጥበቃ ቁጥጥርና ክትትል አንፃር ለዘላቂ ልማት ያላቸውን አስተዋጽኦ በመመልከት የውሳኔ ሀሳብ ለመንግስት ያቀርባል፤
5. በአካባቢ እንክብካቤና ልማት የተሰማሩ መንግስዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የማኅበረሰቦች ማኅበራትንና መንግስዊ አካላትን ከአካባቢ ጥበቃ አንፃር ያስተባብራል፤
6. በሕግ የተደነገጉ የፌዴራሉ የአካባቢ ደረጃዎች ሳይጣሱ የክልሉን የአካባቢ ደረጃዎች ያዘጋጃል፣ ሲጸድቁም አግባብነት ላላቸው አካላት ያሳውቃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
7. በረሃማነትን ለመከላከልና የተጎሳቆሉ ወይም የተራቆቱ አካባቢዎች ሥርዓተ-ምህ□ር መልሶ ማቋቋም የሚያስችሉ ጥናቶችን ያካሂዳል፣ □ማስ□□ሚያ ስልቶችን ይቀይሳል፣ አግባብ ባላቸው አካላት መተግበሩን ይከተላል፤
8. የደን ምርምር እና ልማት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የምርምር፣ የግብዓት ማባዣ፣ የደን ዕፅዋት ዘር ጥራት ቁጥጥር ማዕከላት እና ላቦራቶሪዎችን ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፤
9. የአካባቢ ሁኔታ□ ለማሻሻል አስተዋፅኦ ሊያደርጉ በሚችል መልክ ማህበረሰቦች የየራሳቸውን □ኃይል ፍላጎት ለማሟላት በአካባቢ ላይ □ሚኖረዉን ተጽዕኖ ለማስቀረት □እንዲችሉ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ጠቀሜታ ያላቸው ልምዶችንና አሰራሮችን ያሰራጫል፤

30.በአንድ ማዕከል አገልግሎት ጣቢያ በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች እንዲመዘገቡ፣ እንዲደራጁ፣ ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲያገኙ፣ የዕድሳትና ስረዛ አገልግሎት □እንዲያገኙ □ሚ□ስችል አሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤

31.በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በየዘርፎቻቸው በማህበር እንዲደራጁ በመ□□□ □□በ□ ትስስር ተጠቃሚ □እንዲሆኑ ማድረግ፤

32.በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ ምክርና የኦዲት አገልግሎት እንዲያገኙ ድጋፍ ማ□ረ□፤

33.በክልሉ የዘርፉን የልማት ስትራቴጂ መመሪያና ደንቦችን ከመተግበር አኳያ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በጥናት በመለየት መፍትሔ መስጠት፤

34.በ□ልሉ በማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የእሴት ሰንሰለት ጥናት በማካሄድ በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት ላይ የተመሠረተ የሥልጠና፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የምክር አገልግሎት እንዲያገኙ ማ□ረ□፤

35.□ሞ□ል ኢንተርፕራይዞችን ምርጥ ተሞክሮዎች በማጥናት፣በመቀመርና በማሠራጨ የዘርፉን ልማት ማ□□፤

36.በክልሉ ወጥ የሆነ የመረጃ ሥርዓት □እንዲደራጅ በማ□ረ□ ለዘርፉ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣በመተንተን፣ በማደራጀትና ለተጠቃሚዎች በማሠራጨት አገልግሎት መስጠት፤

37.በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች የልማት ስትራቴጂ መሠረት ከአነስተኛ ወደ ታዳጊ መካከለኛ የሚሸጋገሩ ኢንተርፕራይዞችን መለየት፤

38.በየደረጃዉ የሚገኙ ኢንተርፕራይዞችን ሂሣብ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ራሱ ወይም እሱ በሚወክለው ሰው መመርመር፤

39.በየደረጃዉ ለሚገኙ ኢንተርፕራይዞች ልማት ምክር ቤት እንዲቋቋም ማድረግ፣ሥራዎችንም ማስተባበር፤

40.የንብረት ባለቤት የመሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ ፤

41.ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተዛማች ተግባሮችን ያከናዉናል፡፡

4. የመንገድ ዲዛይንና ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች የሚመለከቱ የቀድሞ የክልሉ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፤
5. የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ዘርፍን የሚመለከቱ የቀድሞ የእንስሳትና አሳ ሀብት ልማት ኤጀንሲ  መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለክልሉ ግብርናና እንስሳት ሀብት ልማት ቢሮ ተላልፈዋል፤
6. ስለ ሚሊሻያ ጉዳይ የሚመለከቱ የቀድሞ የሚሊሻ ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለአስተዳደርና ፀጥታ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ተላልፈዋል፤
7. የኤች አይቪን ጉዳይ የሚመለከቱ የቀድሞው የኤች አይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ሴክሬታሪያት ጽህፈት ቤትመብትና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለጤና ቢሮ ተላልፈዋል፤
8. የቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ መብትና ግዴታዎች  በዚህ አዋጅ መሰረት ለቴክኒክ ሙያና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ቢሮ ተላልፈዋል፤
9. አስገዳጅ የግብርና ምርቶች ግብይት በግብርናና ገጠር ልማት ቢሮ የነበረዉ በዚህ አዋጅ መሰረት ለንግድ፣ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ተላልፈዋል፡፡

## አንቀጽ 36

## አዋጁ ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልል ምክር ቤት ከፀደቀበት ሐምሌ 27/2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አሶሳ ሐምሌ 27/2010 ዓ.ም

አሻድሊ ሀሰን አልአጀብ
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት
ፕሬዝዳንት